በመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ
የስብሰባ አበልና የማበረታቻ
ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ
(የተሻሻለ)

508/2013

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1. መግቢያ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የልማት ድርጅቶችን ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋት፣ መከታተል፣ በልማት ድርጅቶችና አክስዮን ማህበራት ውስጥ መንግስትን በመወከል የመንግስት ባለቤትነት መብት ለማስከበርና ለመምራት የተቋቋመ ኤጀንሲ ነው።

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ ትኩረት በስትራቴጂክ ዕቅድና በድርጅቱ ተልዕኮ መሳካት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ወጥና ግልፅ በሆነ መንገድ ተጠያቂነትን (accountability) ለማስፈን የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ድርጅቱ ባስገኘው ውጤት ላይ በመመስረትና በሀገር ደረጃ እየተከሰተ ያለውን ተለዋዋጭ የገበያ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት፤ የሥራ አመራር ቦርዱን በማበረታታት የልማት ድርጅቱ በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ የተወዳደሪነት መንፈስ እንዲኖገው ለማድረግ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 445 /2011 አንቀጽ 5 (3) መሠረት ይህንን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

II. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ አበልና የማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር **508/2013** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

III. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ኤጀንሲ"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

2) **"የመንግስት የልማት ድርጅት"** ማለት በኤጀንሲው ስር የሚተዳደር ሆኖ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 2 (1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በሌሎች ሕጎች ወይም በመንግስት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፡፡

3) **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 10/2/ እና አንቀጽ 12 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በበላይነት እንዲመራ፣ እንዲቆጣጠርና ውሳኔ እንዲሠጥ የተቋቋመ የስራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

4) **"ማበረታቻ"** ማለት የልማት ድርጅቶች በእቅዳቸው መሠረት ውጤታማ ሲሆኑ አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ ለቦርዱ የሚከፈል ክፍያ እና ዕውቅና ነው፡፡

5) **"ትርፋማነት"** የሚለካው በሀብት ተመላሽ /Return on Asset/ ሆኖ ከታክስ በፊት የተገኘ ትርፍ ለጠቅላላ ሀብት ተካፍሎ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡

6) **"የፋይናንስ ጤናማነት"** ማለት የአንድ የልማት ድርጅት የአጭር ጊዜ ሀብት (Current Asset) የአጭር ጊዜ ዕዳውን (Current Liability) የመሸፈን አቅም፣ ጥሬ ገንዘብ የሥራ ማስኬጃ ፍላጎቱን የማሟላት አቅም፣ እና የመካከለኛና ረጅም ጊዜ ብድሩን ከገቢው ለመክፈል ያለውን አቅም የሚያሳይ አሃዛዊ ምጣኔ (Debt Ratio) ሊያካትት ይችላል፡፡

7) **"የኮርፖሬት አስተዳደር** /Corporate governance/" ማለት የድርጅቱን ቀጣይ እድገት ለማረጋገጥ፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ለማስፋፋት፣ የድርጅቱን የፋይናንስ ጤናማነት ለማረጋገጥና መልካም ስም ለመገንባት መልካም የሥራ አከባቢ ወይም ሁኔታን፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ሥልጣንና ሃላፊነትን በተገቢው ለመወጣትና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ በድርጅቱ ተፈጻሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎች፣ መዋቅራዊ ግንኙነቶች፣ የአሰራር ሥርዓቶችና የስራ ሂደቶች አካቶ የያዘ እና በኤጀንሲው የፀደቀ መመሪያ ወይም ስርዓት ነው፡፡

8) <u>**የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን**</u>፡-

ይህ መመሪያ ለኤጀንሲው ተጠሪ በሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ነው፡፡ ይሁንና በኤጀንሲው ስር ያሉ የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት የተቋማቱ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከናወን ሆኖ የማበረታቻ እና የአበል ክፍያው ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

2. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት እና የውጤት መመዘኛ መስፈርቶች፡-

2.1 ከማበረታቻ መመሪያ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነቶች፡-

2.1.1 የቦርድ አባላትን ይመድባል፣ ያነሳል፣ ከአባላት መካከል የቦርድ ሰብሳቢ ይሾማል፤

2.1.2 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን ያረጋግጣል፣ ዕቅዶቹን ያፀድቃል፣ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

2.1.3 የልማት ድርጅቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ ለመምራት፣ ለመቆጣጠር፣ ወዘተ የተዘጋጀውን የቦርድ እቅድ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

2.1.4 ለቦርዱ አባላት ሊከፈል የሚገባውን አበል ይወስናል፤

2.1.5 በሌላ ተቆጣጣሪ አካል በተለየ ሁኔታ የተወሰነው ካልሆነ በስተቀር በውጤት ላይ የተመሰረተ ማበረታቻ ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲከፈል በውጪ ኦዲት መሠረት ይወስናል፤

2.1.6 የልማት ድርጅቱን የውጭ ኦዲት ሪፖርት ገምግሞ ያፀድቃል፣

2.1.7 በየድርጅቱ ያሉ ቦርዶችና ማኔጅመንት በሥራ ላይ እንዲውሉ የተላለፉ መመሪያዎችን በመተግበርና ማስተግበር ረገድ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ በውጤቱ ላይ ተመስርቶ የማስተካከያ ዕርምጃ ይወስዳል፤

2.2 የልማት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

2.2.1 በኤጀንሲው ጸድቆ በተላከው የኮርፖሬት ገቨርናንስ ኮድ መሰረት ሥራዎችን ይፈጽማል/ያስፈጽማል፤

2.2.2 በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከድርጅቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ የተወሰደ ግልፅ ዓላማና ግብ ያለው ዓመታዊ ዕቅድ የልማት ድርጅቱ እንዲኖረው ያደርጋል፤

2.2.3 ለዕቅዱ ተግባራዊነት የቦርዱን እና የዋና ሥራ አስፈጻሚውን ሚናና ኃላፊነት በግልፅ ለይቶ ያስቀምጣል፤

2.2.4 የልማት ድርጅቱን እቅድና ዓላማ ለማሳካት የቦርድ ንኡሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ እቅድ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣ ያጸድቃል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፤

2.2.5 ቦርድ የልማት ድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ እና የማኔጅመንት አባላት የሚመዘኑበትን መስፈርት በኤጀንሲው ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የሚውለውን "የሥራ አመራር ቦርድ አፈጻጸም ግምገማ መመሪያን" መነሻ በማድረግ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

2.2.6 የልማት ድርጅቱን አፈጻጸም ይገመግማል፣ ለአፈፃፀሙ የቦርዱን ሚና/አስተዋፅኦ እና የተገኘውን ውጤት እንደ ቡድንና እንደግለሰብ በመገምገም ይለያል፣ በቀጣይ መሻሻል በሚገባቸውን ጉዳዮች ላይ በወቅቱ እርምጃ ይወስዳል፤

2.2.7 የቦርድ አባላትን እና የዋና ሥራ አስፈጻሚውን ግምገማና ምዘና በዓመት ሁለት ጊዜ ያካሂዳል፤ የምዘናው ውጤት ለኤጀንሲው ሪፖርት ያደርጋል፤

2.2.8 የድርጅቱ ወቅታዊ ሂሳብ ተዘግቶና በውጪ ኦዲተር ተመርምሮ በጊዜ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤

2.2.9 የዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የማኔጅመንት አባላት ማበረታቻ በውጤት ላይ ተመሥርቶ እንዲፈፀም ያደርጋል፣ ተጠያቂነትን ያሠፍናል፤

2.2.10 ስለድርጅቱና ስለቦርዱ ዕቅድ አፈጻጸም በየሩብ ዓመቱ ለኤጀንሲው የተሟላ ሪፖርት ያቀርባል።

2.3 የውጤት መመዘኛ መሥፈርቶች እና የሚይዙት ክብደት፡-

2.3.1 ምዘናው የሚከናወነው በበጀት ዓመቱ በኤጀንሲው በፀደቁ የግቦች አፈፃፀም መሠረት ይሆናል፤

2.3.2 እንደ ኢንዱስትሪው ባህሪ የለውጥ መሳሪያዎችና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች ተዘጋጅተውና ታቅደው የተፈጸሙትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

2.3.3 የምዘና ማጠቃለያ የሚዘጋጀው በሚከተሉት አራት ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያ (KPI) መስፈርቶች መሰረት ይሆናል፤

2.3.3.1 **የኮርፖሬት አስተዳደር አፈፃፀም** (10%)

- በኤጀንሲው እና እንደአግባቡ በሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት (Regulatory Bodies) ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ በዋለው የኮርፖሬት አስተዳደር ኮድ መሰረት ድርጅት መምራት (10%) ፤

2.3.3.2 **ለትርፋማነት እና የፋይናንስ ጤናማነት አፈጻጸም የሚሰጠው ክብደት (60%) የሚይዝ ሆኖ፡-**

ሀ) ለትርፋማነት (Return on Asset) **የሚሰጠው ክብደት** (45%) ፤

ለ) የፋይናንስ ጤናማነት (15%)፡-

- Current ratio (5%)፤
- Debt ratio (10%)፤

2.3.3.3 **የድርጅትን ቀጣይ ዕድገት የሚያረጋግጥ ሥራ የሚይዘው ክብደት /15%/ ሆኖ፡-**

ሀ) የአሰራር ስርአትን ማዘመን እና ዲጅታላይዜሽንን መተግበር /3%/፤

ለ) የሥጋት ሥራ አመራር /3%/፤

ሐ) የገበያ አድማስ ማስፋት (ወጪ ንግድን ጨምሮ) /3%/፤

መ) የሰው ኃብት ልማት /2%/፤

ሠ) ስርዓተ ጾታን ያገናዘበ ተኪ አመራር ማፍራት /2%/፤

ረ) ምርምር፣ ስርጸትና አዳዲስ/የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም /2%/፤

2.3.3.4 **ድርጅቱ መወጣት ያለበትን ግዴታና የባለድርሻ አካላትን መብትና ጥቅም ማክበር /15%/ የሚይዝ ሆኖ፡-**

ሀ) የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነትን አቅዶ መወጣት /2%/፤

ለ) ወቅታዊ የተሟላ ዲስክሎዠር /2%/፤

ሐ) በወቅቱ ሂሳብ ዘግቶ ማስመርመር /5%/ የሚይዝ ሆኖ ያለፈውን የበጀት ዓመት ሂሳብ በቀጣዩ ዓመት፤

- እስከ ጥር 30 አስመርምሮ ላቀረበ /5%/፣
- እስከ መጋቢት 30 አስመርምሮ ላቀረበ /3%/፣
- ከሚያዚያ እስከ ሰኔ 30 አስመርምሮ ላቀረበ /2%/ ነጥብ የሚሰጥ ይሆናል።

መ) የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ መፈጸም /4%/፤

ሠ) ብድር አመላለስ (2%) ይይዛል፤

ክፍል ሦስት

3 የቦርድ ወርሃዊ የስብሰባ ክፍያና ዓመታዊ የማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም፤

3.1 ወርሃዊ የቦርድ የስብሰባ አበል ክፍያ አፈጻጸም፤

3.1.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ደረጃ ለመወሰን በወጣው "የልማት ድርጅቶች የደረጃ አሰጣጥ መመሪያ" መሰረት ድርጅቶች በወጣላቸው ደረጃ የሚለዩ በመሆናቸው የቦርድ አባላት የስብሰባ አበል ክፍያ እንደ ድርጅቱ ደረጃ ይለያያል፤

3.1.2 ቦርድ የልማት ድርጅቱን አፈጻጸም ለመከታተል፣ ለመገምገም እና አቅጣጫ ለመስጠት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለሚያደርገው ስብሰባ አበል ይከፈለዋል፡፡

3.1.3 የቦርድ ንዑሳን ኮሚቴዎች እንደ ቦርድ አባል ከሚያገኙት አበል በተጨማሪ የንዑስ ኮሚቴ ስብሰባ ባካሄዱ ጊዜ የአንድ ስብስባ ተጨማሪ ክፍያ ይደረግላቸዋል፡፡

3.1.4 በወር ውስጥ ቦርድ ወይም የቦርድ ንኡሳን ኮሚቴ አባላት ካልተሰበሰቡ እንዲሁም በወሩ በስብሰባ ላይ ላልተገኙ የቦርድ ወይም የንኡሳን ኮሚቴ አባላት ላልተገኙበት ስብሰባ አበል አይከፈልም፡፡

3.1.5 የቦርድና የንኡሳን ኮሚቴዎች ወርሃዊ የስብሰባ አበል ክፍያ ከታች በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

የቦርድ አባላት ወርሃዊ የሰብሰባ አበል ክፍያ መጠን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ደረጃ	ወርሀዊ የክፍያ መጠን "በብር"					
		ለቦርድ ሰብሳቢ	ለቦርድ አባል	የቦርድ ፀሐፊ	ለን/ኮሚቴ ሰብሳቢ	ለን/ኮሚቴ አባል	ለንኡሳን ኮሚቴ ፀሐፊ
1	የአንደኛ ደረጃ	8,000	6,000	3,000	1,500	1,000	1,000
2	የሁለተኛ ደረጃ	7,000	5,000	3,000	1,500	1,000	1,000
3	የሶስተኛ ደረጃ	6,000	4,000	3,000	1,500	1,000	1,000

3.1 የማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም፡-

3.1.1 የማበረታቻ ክፍያ በአፈፃጸም ግምገማ ውጤታቸው ከ95% በላይ ላስመዘገቡ ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከዚያ በታች እስከ 80% ድረስ ውጤት ላስመዘገቡ አባላት በየደረጃው ተሰልቶ የሚከፈል ሲሆን ዝርዝሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3.2.1 ተመላክቷል፤

3.1.2 የማበረታቻ ክፍያ በአንድ የበጀት ዓመት ከ6 ወራት በታች ላገለገለ የቦርድ አባል አይፈጸምም፤

3.1.3 አፈፃፀሙ በተመዘገበበት የበጀት ዓመት ከ10-12 ወራት የሰሩ እንደ አፈጻጸማቸው ተሰልቶ 100% የሚያገኙ ሲሆን ከ 6-9 ወር ያገለገሉ የቦርድ አባላት የማበረታቻውን ክፍያ 75% የሚያገኙ ይሆናል፡፡

3.1.4 የማበረታቻ ክፍያ ሊከፈል የሚችለው በውጭ ኦዲተር በተመረመረ ሂሳብ ላይ በመመሥረት ይሆናል፤

3.1.5 የተመረመረው ሂሳብ ሪፖርት የድርጅቱን ሁኔታ በትክክል እንደማያሳይ (Disclaimer or Adverse opinion) የሚገልጽ ከሆነ ማበረታቻ ክፍያ አይፈፀምም፤

3.1.6 የድርጅቱን የተሟላ አፈጻጸም የሚያሳይ ሪፖርት ለኤጀንሲው በወቅቱ የማያቀርብ ሥራ አመራር ቦርድ የማበረታቻ ክፍያ አያገኝም፤

3.1.7 የማበረታቻ ክፍያ የሚከፈለው ድርጅቱ ትርፋማ ከሆነ ወይም በእቅዱ መሰረት ኪሳራውን የቀነሰ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

3.1.8 የማበረታቻ ክፍያ የሚፈጸመው በኤጀንሲው በኦፕሬሽን ዘርፍ አማካይነት ዓመታዊ የልማት ድርጅቱ አፈጻጸም ተገምግሞና ለማበረታቻ ክፍያ ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ ቀርቦ በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ከጸደቀ በኋላ ለድርጅቱ በጽሁፍ ሲገለጽ ብቻ ይሆናል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency

3.2 የማበረታቻ ክፍያ መጠን

3.2.1 ለቦርድ አባላት የሚሰጥ ማበረታቻ ክፍያ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

የልማት ድርጅቱ ደረጃ	በጣም ከፍተኛ ውጤት ከ95% በላይ		ከፍተኛ ውጤት ከ91-95%		አጥጋቢ ውጤት ከ86-90%		መሻሻል ያለበት ውጤት ከ80-85%	
	ሰብሳቢ	አባል	ሰብሳቢ	አባል	ሰብሳቢ	አባል	ሰብሳቢ	አባል
ደረጃ 1	75,000	67,500	67,500	61,000	61,000	55,000	55,000	50,000
ደረጃ 2	67,500	61,000	61,000	55,000	55,000	50,000	50,000	45,000
ደረጃ 3	61,000	55,000	55,000	50,000	50,000	45,000	45,000	40,000

3.3 ዓመታዊ የማበረታቻ ክፍያ በተጨማሪ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ማበረታቻዎች፡-

3.3.1 የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የቦርድ አባላት ከመደበኛ ማበረታቻ ክፍያ በተጨማሪ ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፣ ይህም በኤጀንሲው በሚዘጋጀው ልዩ የሽልማት እና እውቅና ስርዓት የሚፈፀም ሆኖ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤

ሀ) የተሻለ ውጤት ያስገኙ ድርጅቶች በዓመታዊ መጽሔቶች፣ ድረ ገጽ እና ሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲተዋወቁ ሊደረግ ይችላል፤

ለ) የተመረጠ የውጪ ሀገር የላቀ ተሞክሮና ልዩ ሥልጠና እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ማበረታቻዎች እንዲያገኙ ሊደረግ ይችላል፤

4 የተሻረ መመሪያ

ሰኔ 19 ቀን 2010 ዓ.ም የወጣው "**የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የቦርድና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ግምገማና ማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ**" በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

5 መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

6 መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

በየነ ገ/መስቀል

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

አባሪ 1፤ የድርጅት ውጤት መመዘኛዎች ማጠቃለያ

ተ.ቁ	መመዘኛ	የሚይዘው ክብደት /በመቶኛ/
1	**የኮርፖሬት አስተዳደር አፈፃጸም** - በኤጀንሲው እና እንደአግባቡ በሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት (Regulatory Bodies) ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ በዋለው የኮርፖሬት አስተዳደር ኮድ መሰረት ድርጅት መምራት፤	10%
2	**ትርፋማነት እና የፋይናንስ ጤናማነት አፈጻጸም**	60%
2.1.	**ትርፋማነት** /Return on Asset/	45%
2.2	**የፋይናንስ ጤና** - Current ratio (5%)፣ - Debt ratio (10%)፣	15%
3	**የድርጅትን ቀጣይ ዕድገት የሚያረጋግጥ ሥራ**	15%
	- የአሰራር ስርአትን ማዘመን እና ዲጅታላይዜሽንን መተግበር (3%)	
	- የስጋት ሥራ አመራር (3%) ፣	
	- የገበያ አድማስ ማስፋፋት (ወጪ ንግድን ጨምሮ) (3%)	
	- የሰው ኃብት ልማት (2%)	
	- ስርአተ ጾታን ያገናዘበ ተኪ አመራር ማፍራት (2%)	
	- ምርምር፣ ስርጸት እና አዳዲስ/የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም (2%)	
4	**ድርጅቱ መወጣት ያለበትን ግዴታና የባለድርሻ አካላትን መብትና ጥቅም ማክበር** - የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነትን አቅዶ መወጣት (2%)፤ - ወቅታዊ የተሟላ ዲስክሎዠር (2%)፣ - በወቅቱ ሂሳብ ዘግቶ ማስመርመር (5%) ፣ - የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ መፈጸም (4%)፤ - ብድር አመላለስ (2%)፤	15%
	ድምር	100%

<u>ማስታወሻ፡-</u>

- የድርጅቱ አጠቃላይ ውጤት 60% ክብደት ይይዛል፣
- የቦርድ ምዘና ውጤት 40% ክብደት ይይዛል፣
- የመጨረሻ የቦርድ ምዘና፡- 0.40 (የቦርድ ውጤት ከመቶ) + 0.60 (የድርጅቱ አጠቃላይ ውጤት ከመቶ) የሚገኘው ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Public Enterprises Holding and Administration Agency